የያሬድ ውብ ዜማ ድንግል እመቤቴ ስጦታዬ ነሽ/2/
በምን አንደበቴ እንዴትስ ባለ ቃል ማርያም ልበልሽ/2/
ምድርና ሰማዩ ተአምርሽን ይንገሩ
ፍጥረታት በሙሉ ስለአንቺ ይመስክሩ
ተነግሮ የማያልቅ ድንቅ ነው ስራሽ
ድንግል ሆይ እናቴ አምሳያ የለሽ
ማርያም ድንግል እረዳቴ
የምትደርሽልኝ ነይ ስልሽ በጭንቀቴ
ታምርሽንም በአይኔ አይቻለሁ
ጽዮን ሆይ ስልሽ ድንግል ሆይ እጠግባለሁ
የያሬድ ውብ ዜማ.....
የእግዚአብሔር ጥበቡ በአንቺ ተገለጠ
የአዳም ዘር በሙሉ ከሞት አመለጠ
የመዳን ምክንያት ማርያም አንቺ ነሽ
ለፍጥረታት ሁሉ መሰላል የሆንሽ
ነገን ባላውቅ እኔንም ቢያስፈራኝም
አንቺ ካለሽ በፍፁም አልወድቅም
በፊትሽም እንድቆሞ በምስጋና
ማርያም ልበልሽ በትህትና
የያሬድ ውብ ዜማ .....
ትውልዱ በሙሉ ለምስጋና ይቁም
ባንቺ ስለሆነ የቀረለት መርገም
አዳም ከነልጁ በሰማይ በምድር
ማርያም /2/ ይበል ታምርሽን ይናገር
ጨለማውም ከፊቴ ተገፈፈ
ማርያም በምልጃሽ ልቤ አረፈ
ከጎኔ ነሽ ስልሽ እጽናናለሁ
እሳት ገደሉን ሁሉንም አልፈዋለሁ
የያሬድ ውብ ዜማ.....